በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

ታሕሣሥ 16 ቀን 2010 ዓም

## ለነፃነት መሰዋት አኩሪ ታሪክን ለአገርና ለሕዝብ ማስተላለፍ ነው!!
## ትግሉ ሳያቋርጥ ተፋፍሞ ይቀጥል።

ለአንድ አገር ስልጣኔና እድገት ትምህርት የሚጫወተው ሚና ትልቅ ነው። የትምህርቱን ስራ ተግባር ላይ ለማዋል መምህራን፣ ተማሪዎች ፣ ወላጆችና የትምህርት ባለደርሻዎች (Stake-holders) የሚኖራቸውም አስተዋጽኦ ሚዛኑ ከባድ ነው። በአገራችን ኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት መሰጠት ከተጀመረበት ከ19ኛው ምዕተ ዓመት ኢጋማሽ ጀምሮ መምህራን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች ዘመናዊ ትምህርትን በጥራት ለማዳረስ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። ሰብአዊና ዲሞክራዊ መብቶች እንዲከበሩ ብዙ ትግል ሲያደርጉ ቆይተዋል።የሕብረተሰቡ አካል በመሆናቸውም ከሕዝብ ጎን በመቆም የሕዝብ ጥያቄዎችን በማንሳት ታግለዋል። አሁንም እየታጋሉ ነው። ይህን በማድረጋቸው በመምህራንና በማህበራቸው ኢመማ ላይ ብዙ ግፎች ተፈጽመዋል። በዚህ መግለጫ ላይ መምህራን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመቆም የከፈሉትን ታላቅ የሕይወት መስዋዕትነትና ለአገርና ለሕዝብ የሚያስተላልፉትን መልዕክቶችን በአጭሩ እንጠቅሳለን።
የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የጣሊያን መንግስት የቤኔቶ ሞሶሎኒ ወኪል የነበረው ፋሽስት ግራዚያኒ አዲስ አበባ ከተማ በገነተ ልኡል ቤተመንግስት ውስጥ ሕዝብ ሰብሰቦ በመደንፋት ንግግር ሲያደርግ በነበረበት ወቅት ፋሽስቱን ለመግደል ቦንብ የወረወሩት ጀግኖቹ አብርሃ ዶቦጭና ሞገስ አስገዶም መምህራን ነበሩ።

ሰኔ 7 ቀን 1929 ዓም በሮም ከተማ ውስጥ ፋሽስቱ የጣሊያን መንግስት አገራችንን በመውረሩ በመደሰትና በተለያዩ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሞቱት ለፋሽስት ወታደሮቹ ክብር ለመስጠት በአዘጋጀው በዓል ላይ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ መሬት ላይ ጥሎ በዓሉን ለማክበር የወጣው ሕዝብና ወታደሩ ሰንደቅዓላማውን እንዲረግጡና ምራቅ እንዲተፉበት ሲያደርግ በዚያው በጣሊያን አገር የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ስር የቅርስ ጥበቃ ክፍል ሰራተኛ የነበሩት ፣ ጣሊያን ከኢትዮጵያ ወስዶ በቅርሱ ክፍል ያስቀመጠውን የራስ አሉላ አበነጋ ጎራዴ በመያዝ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ ከወደቀበት አንስቶ በአንጋቱ ላይ በመጠምጠም በንዴትና በፉካራ በያዛው ጎራዴ ጣሊያኖችን አንጋታቸውን በመቀንጠስ የሮም ከተማን ያሸበረው በዕለቱ በጣሊያን ጥይት የተመው፣ በኋላም በጣሊያን እስር ቤት በመርዝ የተገደለው ጀግናው ዘርዓይ ደረስ በኢርትራ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር ነበረ። ወደ ጣሊያንም የሄደው መምህር በመሆኑና አማርኛ ፣ ጣሊያንኛና እንግሊዝኛ ስለሚችል ጣሊያን ከኢትዮጵያ ወስዶ ሮም ውስጥ ያሳራቸውን ኢትዮጵያዉያዊ ወገኖቹን በትርጉም ስራ ለማገልገል ነበር።
በ1967 ዓም በጠመንጃ ኃይል ከህዝብ ሥልጣን የቀማውን የምርጥ መኮንኖች መንግስትን በመቃወም ከሕዝብ ጎን በመቆም፣ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን የድሃ ልጅ ይማር፣ ትምህርት ፖሊሲው በባለሙያዎች ይቀረጽ፣ መሬት ላራሹ፣ የሃይማኖት ዕኩልነት ይሰፈን ፣ ዲሞክራሲ ያለገደበ አሁኑኑ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም ሌሎች ጥያቄዎችን በማንሳትና ለተግባራዊነቱም በመታጋላቸው ብዙ መምህራንና የኢመማ መሪዎች የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። ለእስር፣ ለእንግሊትና ለስደት ተዳርገዋል።

ፋሽስት ደርግን የተካው ወያኔ የተባለው የዘር መድልዎ ስርዓት አራማጅ የማፊያ ቡድን በውጭ ኃይሎች እርዳታ በስልጣን ላይ ከወጠበት ጊዜ ጀምሮ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲና የመብት ረገጣን በመቃወማቸው መምህራን ላይ መጠነ ሰፊ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል። አገዛዙ መምህራንን፣ ተማሪወችን፣ወላጆችን፣ የትምህርት ባለሙያዎችን ሳያሳትፍ በዓለም አቀፍ የገንዘብ አባዳሪ ድርጅት በመታገዝ ትውልድ ገዳይ የትምህርት ፖሊሲ በመቅረጹ ፖሊሲውን ይቃወማሉ ፣ ለትምህርቱ ጥራት ይቆማሉ የሚላቸውን መምህራን ለማጥቃት የመጀመሪያውን እርምጃ የወሰደው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 42 ፕሮፌሰሮችን በማባረር ነበር። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ ለትምህርቱ ጥራት፣ ለመምህራን፣ ለሕዝብ መብትና ጥቅም የቆሙትን መምህራን በጥይትና በሌሎች የግድያ ዘዴዎች ሕይወታቸው እንዲጠፉ አድርጓል።

ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም ከቤቱ በሰላም ወጥቶ ወደ ስራ ወደ ኢመማ ጽ/ቤት ይሄድ የነበረው የኢመማ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የታሪክ መምህር አሰፋ ማሩ በአዲስ አበባ ከተማ በሐምሌ 19 የሕዝብ መነፈሻ አከባቢ በወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ሕይወቱን አጥቷል። መምህር አሰፋ ማሩ ትምህርት በጥራት ለሕዝብ ልጆች እንዲዳረስ ለመምህራን መብት መከበር የታጋለ ምሁር ነበር።

*ሕዳር 6 ቀን 2004 ዓም በደዋሮ ዞን በዋካ ከተማ የዋካ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ መምህር የነበረው የኔሰው ገብሬ በሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን በደል አላይም በማለት በራሱ ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍና እሳት በመለኮስ ራሱን ሰዉቷል። እንዲሁም በሀዲያ ዞን በጊምቢቹ ወረዳ በሁመሮ ትምህርት ቤት የሲቪክስ መምህር የነበረው የ23 ዓመት ወጣት ጌታቸው አብርሃም በራሱና በሕዝቡ ላይ የሚፈጸመውን በደል በመቃወም በወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት እሁድ ሚያዝያ 17 ቀን 2007 ዓም በራሱ ላይ ጋዝ በማርከፍከፍ ህይወቱን አጥፍቷል።*

*ሕዳር 24 ቀን 2010 ዓ.ም በወልዲያ ከተማና በመቀሌ ከተማ የእግር ኳስ ቡድኖች መካከል በ9፡00 ሰዓት ሊደረግ ታቅዶ በነበረው ጨዋታ ወቅት የመቀሌ ከተማ ቡድን ደጋፊዎች በወልዲያ ሕዝብ ላይ አስጸያፊ ስድብ በመሰዳባቸው ምክንያት ሕዝቡ ቁጣውን በማሳማቱ የወያኔ የአጋዚ ጦር በሕዝብ ላይ በከፈተው የእሩምታ ተኩስ ከተሰውት ሶስት ወገኖች መካከል መምህር ታምሩ በሪሁን ይገኝበታል። መምህር ታምሩ ትውልድ ቦታው ጎጃም ሲሆን ዘመዶቹ አስካሬኑን ወደዚያው ለመውሰድ ሲጠይቁ የወልዲያ ሕዝብ ለእኛ ሲል የተሰዋ ስለሆነ እኛው ጋ ለታሪክ ማስታወሻነት ይቀበራል በማለት መላው የወልዲያና የአካባቢው ሕዝብ እንዲሁም በወልዲያ የሚገኙ መምህራን በተገኙበት በከፍተኛ ቁጭት የቀብር ስነሥርዓቱ ተፈጽሟል። ይህ በመምህር ታምሩ ላይ የተፈመው የግፍ ግድያ በህዝብ መካከል አንድነትን የፈጠረ ጠላቱን ወያኔ ቆርጦ እንዲተጋል ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው።*
*ሕዳር 2 ቀን 2010ዓም በአዲስ አበባ ስታዲየም ውስጥ በተተከለው የመብራት ፓውዛ ማማ ላይ በመውጣት ወያኔ የአገራችን መለያ በሆነው ሰንደቅዓላማ ላይ የለጠፈመው የሴይጣን ተከታዮች ምልክት የሆነው የሌለበትን አረንጓዴ፣ቢጫ ፣ ቀይ ብቻ ያለበትን ሰንደቅዓላማ በመብራት ምሶሶው ላይ ሶስት ቦታ በመለጠፍና ለሰዓታት በማውለብለብ ራሱም ሰንደቅዓላማውን በመልበስ ወያኔ በሕዝብ ላይ የፈጸመውን በደል የተቃወመው ወጣት ዋሲሁን ኢያኖ መምህር ነው። በሮም አደባባይ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ በመያዝ ጣሊያኖችን በጎራዴ አንጋቸውን የቀጠነሰው ጀግናው ዘርዓይ ደረስን በጥይት መተው የበለጠ መረጃ ለማግኘት ሀኪም ቤት በመወሰድ እንዲድን ካዳረጉ በኋላ እስር ቤት ነበር የከተቱት በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ተላላኪ የሆነው ወያኔም ጀግናውን መምህር ዋሲሁንን በፖሊሶችና በእሳት አደጋ ሰራተኞች አማካይነት በመለማመጥ በክሬን እንዲወርድ ካደረገ በኋላ ሕዝብ ወደ ሚሳቃይበት ወደ ሶስተኛ ማዕከላዊ ምርመራ ክፍል ወስዶ ነበረ ያሰረው።*

*ከላይ ስማቸውን የጠቅስናቸው ጥቂት መምህራን ለነፃነት መሰዋት የሆኑ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አኩሪ ታሪክ ያስተላለፉ ናቸው። አርአያናታቸውን መምህራን ሊከተሉ ይጠበቅበቸዋል።*
*በስደት የኢትዮጵያ መምህራን አስተባባሪ ኮሚቴ ለሚወዷት አገራቸውና ለሕዝብ ሲሉ ሕይወታቸውን ለሰው መምህራን ከፍተኛ አክብሮት እያሰጠ በዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ስር እየማቀቀች የምትገኛውን አገራችንን፤ መብት አልባ የሆነውን ሕዝባችንን፣ የአገሪቱን ታሪክና ወደፊትም አገሪቷ ታሪክ እንዳይኖረት የታሪክ ትምህርት እንዳይሰጥ እያደረገ ካለው ከጥቂት ዘረኞች አገዛዝ ነፃ ለመውጣት መምህራን ፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሰራተኞች ፣ ገበሬዎች፣ ወታደሮች ፣ --ወዘተ በመተባበር ተፋፍሞ ያለውን ሕዝባዊ ትግል ሳይቋረጥ እንዲቀጥል ጥሪ ያቀርባል። ለአገርና ለሕዝብ ነፃነት መሞት ክቡር ነው።*

*የወያኔ አጋዚ ጦር በምስራቅ ሐረርጌ በጨለንቆ ሕዝባችን ላይ የወሰደውን ግድያ በማውገዝ ገዳዩ የአጋዝ ጦር አዛዦች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ በተለያዩ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የአጋዚ ጦር የፈጸመውን ግድያ፣ ድብደባ፣ እስራትና የትምህርት ሂደት ማደናቀፍን በጥብቅ ያወግዛል። በየዩኒቨርሲቲዎቹ በፀጥታ ማስከበር በሚል ሰበብ የወያኔ ነፍሰ ገዳይ አጋዚ ጦር መስፈርን ይቃወማል።በአስቸኳይ የሰፈረው የአጋዚ ጦር እንዲወጣ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባባሪ ኮሚቴ አጥብቆ ይጠይቃል። የአንደኛ፣ የመለስተኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጎን እንዲቆሙና በትግሉም እንዲሳታፉ ማህበሩ ያሳስባል። እንድነት ኃይል ነው፤ ተባበሩ።*

*መተባበር፣ መተባበር፣መተባበር፣ መደራጀት፣ መደራጀት ፣ መደራጀት!!*
*ጸረ-ሕዝቡ የወያኔ አገዛዝ በተባበረ የሕዝብ ትግል ይወገዳል!!*
*ለአገርና ለሕዝብ ነፃነት መሰዋት ጀግንነት ነው!!*
*የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!*